# ከብዛት ጥራት፣

ከማተቤ መለሰ ተሰማ፡

ዴንማርክ በተካሄደው፡ የዓለም አየር ንብረት፡ ጥበቃ፡ ጉባዔ ላይ፡ ሕዝብንም፣ ታሪክንም፣ እግዚያብሔርንም፡ የካደው፣ የናቀውና የረገጠው፡ ዘረኛውና፡ የነፍሰ ገዳዩ የመለስ ዜናዊን፡ መሣተፍ፡ በመቃወም በአውሮፓ፡ የሚኖሩ ኢትዩጵያውያን፡ በኮፐን ሀገን፡ ከተማ ተገኝተው፡ በ17 እና 18/ 12/ 09 ድምጹን ለታፈነው፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ ድምጽ በመሆን፡ በሚያስገርም፡ ጽናት ጩኸቱን ለዓለም መሪዎችና ሕብረተሰብ፡ ሲያሰሙ ሰንብተዋል።

እኔም ለዚህ ሰልፍ ታዳሚ ሰለነበርሁ፡ በብዙ ሚድያዎች የተዘገበ ስለሆነ፡ ጊዜን ከመቆጥብ አንጻር፡ ዝርዝር ውስጥ ሣልገባ፡ ዴንማርክ ከሚኖሩ ኢትዩጵያውያን መካከል ለአይን ጥቂት የሚባሉ፡ በተግባር ግን ሺዎች፡ ያደረጉትን ሁለንተናዊ፡ እንቅስቃሴና ለሰልፉ መሣካት፡ የከፈሉትን የአዕምሮ፣ የጉልበት፣ የጊዜና የገንዘብ መሷዕትንት፡ እንዲሁም ያስገኙትን አመርቂ ውጤት ስመለከት፡ በየትኛውም እንቅስቃሴ፡ የውጤት ባለቤት ለመሆን፡ ወሣኙ ብዛት ሣይሆን ጥራት፡ መሆኑን የበለጠ እንድገነዘብ አድርጎኛል።

እነኝህ በቁጥር ጥቂት፡ በተግባር ግን ሺዎች፡ የሆኑ ወገኖቻችን፡ የሰልፉን ቦታ ከማስፈቀድ ጀምሮ፡ ከእየሀገሩ የሚመጡ ኢትዩጵያውያንን፡ ተቀብሎ አጠቃላይ መሥተንግዶ፡ በማድረግ ያከናወኑት የተቀዳጀ፡ ሥራ ለሌሎቻችንም፡ በአርያነት ሊያስተምረን የሚችል ነው፡ ብየ አስባለሁ።

በተለይ 17 ለ 18 አጥቢያ፡ ባደረጉልን የእራት ግብዣ ምሽት ላይ ሁሉም ተሰብሣቢ፡ ፍቅርን፣ መተባበርንና፡ መናበብን ከእነሱ የተማረ፡ በሚመስል አኳኋን፡ ሳይነጋገር በእይታ ሲግባባ ነበር፡ያመሸው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል በርካታ ኢትዮጵያውያን፡ በአየር፣ በይብስ፣ በባህር፣ ተጉዘው፡በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች አቋርጠው፡ ሰልፉላይ ሲገኙ፡ ኮፐን ሀገን ከተማ እየኖሩ፡ ለስልፉ መሣካት አስተዋጾ ማድረግ አይደለም፡ ወደሰልፉ ያልመጡ ኢትዩጵያውያን እንዳሉ ሥሠማ፡ ከማሣዘንም አልፎ አስገርሞኛል፡ ስለሀቅ ምንም ይሁን ምን፡ ማሸነፋቸው የማይቀረው፡ እውነትና ህዝብ፡ የድል ባለቤት ሲሆኑ፡ እነዚህ አርበኛውና ባንዳው ከሚተላለፍበት መንገድ ላይ በመቆም፡ ለሁለቱም ድንጋይ በማቅበል፡ ላይ ያሉ መሀል ሰፋሪዎች፡ ምን እየሰራን ነበር ይሉን ይሆን? ማን ያውቃል፡ አፍያለው ጤፍ ይቆላል ይባል የለ፡ አያፍሩምና ቀድመው ለመገኜት፡ መሞከራቸው አይቀርም ለዚያ ሰው ይበለንና ለማይት ያብቃን፡ ከማለት ሌላ የምለው አይኖረኝም።

የኮፐን ሀገን አየር ደግሞ፡ ከመለስ ጋር የተማከረ፡ ይመሥል መብረድ ሣይሆን የሚለበልብ፡ አይነት ነበር፡ እኔማ ጀርመን የሚኖሩ ኢትዩጵያውያን፡ ይዘውት የመጡት መኪና ባይኖር፡ ደርቄ መገኜቴ የማይቀር ነበር፡ 2 ካልሲ 2 ሱሪ 3 ተደራቢ ልብስና ካፓርት፡ ለብሸና 2 የብርድ ኮፍያ በእራሴ ተሸክሜ ምንም ልቋቋመው አልቻልኩም፡ አንድ የገረመኝ፡ ነገር ቢንኖር፡ አጠገባችን የተሰለፉ፡ ቻይናዎች፡ ጫማቸውን አውልቀው፡ በባዶ እግራቸው ቆመው፡ ያንን ሁሉ ስአት ሲያሣልፉ፡ አልመውደቃቸውን ማያቴ ነብር፡ በእውነት በሁለት፡ አመት የአውሮፓ፡ ቆይታየ ሀይለኛ ብርድ ያየሁበት ጊዜ ቢኖር የኮፐንሀገኑ 2ኛየ ነው፡ አንደኛው አምና በዚህ ወር መግቢያ ላይ፡ ቴዲ አፍሮ፡ እስር ቤት በነበረበት ወቅት ይፈታልን፡ በማለት በኖርወይ የሚኖረው፡ ኢትዩጵያዊያን፡ በኦስሎ ከተማ፡ ሰላማዊ ሰልፍ ባደረገበት ዕለት ልክ እንደዝንድሮው ኮፐን ሀገን ከተማ ብርዱ አንጀት ውስጥ ገብቶ የሚያንሥፍስፍ ነበር፡ ዛሪግን ቴዲ ያንን ቁር ሣይበግረው የጮኸለትን ብዙሀን የኖርወይ ነዋሪ ህዝብ፡ በሚያሣዝን ሁኔታ፡ ሲዘልፈው ተስተውሏል፡ ነገርን ነገር ያነሣዋል ነውና፡ ካነሣሁት አይቀር፡ አርተስቱ ከኢትዩጵያ ዛሪ ድህረገጽ ኖርዎይን አስመልክቶ፡ ለቀረበለ ጥያቄ የሰጠውን መልስ፡ ከእነአንደምታው እንደሚከተለው፡ እንቃኜው።

ጋዜጠኛ ያሪድ ቴዲን ኖቬንበር 28 የተካሄደውን፡ የኖርወይ፡ ኮንሰርትህን፡ ቦይ ኮት ለማድረግ የተንቀሣቀሱ፡ ሰዎች ነበሩ ይባላል፡ እንዴት ነው? ሲል ላቀረበለት ጥያቄ ሲመልሥ፡ ከአንድ ሺህ በላይ ሰው ነው የገባው፡ ይሄ የተባለውም፡ ነገር መሰረት የሌለውና ፍፁም መስመር የሣተ፡ በጣት የሚቆጠሩ ሠዎች፡ እንቅስቃሴ ነው ነበር ያለው። ከዚህ ቃለምልልሥ፡ ላይ በሀሰት ካባ የተጀቦኑትን፡ ነጥየ በማውጣት የእውነትን ጽሀይ ለማሞቅ አንድ ሁለት ልበል።

1ኛ/ አርተስቱ 1000 በላይ ሰው፡ ሙዚቃየን ተከታትሎታል፡ ብሏል እውነቱ ግን የተከራዩት አዳራሽ፡ 1000 ሰው ቀርቶ 500 ሰውም አያስተናግድ፡ የገባው ሰው ከ300 አይበልጥም፡ ይኸውም ኢትዩጵያዊ ብቻ ሣይሆን፡ በአብዛኛው ኢትዮጵያ የተወለዱ፡ ኤርትራውያንና በኤርትራዊነት ሥም ጥገኝነት የጠየቁ የትግራይ አካባቢ ተወላጅ የወያኔ ደጋፊዎች፡ እንዲሁም ኢትዩጵያ ውስጥ የኖሩ የሶማሊያ ዜጎች ናቸው። ቴዲ ግን በ3 እጥፍ አሣድጎ፡ 1000 ኢትዩጵያዊ ሙዚቃየን ተከታተለው ማለቱ፡ በግሌ ለእሱ የነረኝን አክብሮት፡ እንዳነሣ ማድረግ ብቻ ሣይሆን፡ ማስመሠልና መዋሸት፡ የወያኔ ቀዳሚ መለያዎች ሥለሆኑ ይህ ሰው ወዴት እያመራ ነው የሚለውን፡ ጥያቄ በህሌናየ እንዳብሰለስለው አድርጎኛል።

2ኛ/ ኖርወይ የሚኖረውን፡ ብዙሀን ኢትዮጵያዊ፡ ሲያንቋሸሽና ያለውን ንቀት ሲያንጸባርቅ፡ ደግሞ (መሰረት የሌለውና መሥመር የሣተ፡ በጣት የሚቆጠሩ፡ ሰዎች እንቅስቃሴ ነው) ነው ያለው እሱ እሥር ቤት በነበረበት ወቅት፡ በዝናብና በበረዶ እየተደበደበ፡ በብርድ እየተጠበሰ፡ ቴዲ ወንጀለኛ አይደለም በማለት ሲጮህለት የነበረው ዛሬ ትቂት እያለ የሚዘልፈው፡ ህዝብ ነበር፡ አሁን አብሮአቸው የሚጨፍረው እነአቶ ደሥታ ገ/ ስላሴ እማ መፈታት የለበትም ነፍሰ ገዳይነው በማለት ሲያዎዙት የነበሩ ናቸው። የሚያስገርምው ነገር፡ አርተስቱ ከጠላቶቹ ጋር ተሰልፎ፡ ወገኖቹን መዝለፉ ብቻ ሣይሆን፡ አቶ መለስ ዜናዊ፡ ትቂት መስመር የሣቱ ጽንፈኞች፡ በማለት ኢትዮጵያውያንን፡ ሲያብጠለጥሉበት፡ የኖሩበትን ያነጋግር ዘይቤ፡ በከፊል አሻሺሎ በጣት የሚቆጠና መስመር የሣቱ፡ ማለቱ፡ ወዴት እያመራ እንደሆነ ማሣያ መስታዎት ይመስለኛል። ለማነኛውም እኔ በማህሉ፡ እየኖርሁ የተረዳሁት፡ ኖርወይ የሚኖረው ኢትዩጵያዊ፡ እሱም ሆነ የቆመላቸው ወያኔዎች፡ እንደሚሉት ትቂቶች ሣይሆኑ፡ ብዙዎች መስመር የሣቱ ሣይሆኑ፡ ትክክለኛውን መንገድ ይዘው፡ ነገ ማሸነፋቸው ለማይቀረው፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ እየታገሉ ያሉ መሆናቸውን ነው። እንደእውነቱ ከሆነ መስመር የሣተ እሱእራሱ ነው።

3ኛ/ ጋዜጠኛ ያሪድ በሲዊድንና፡ በኖርወይ፡ የነበረውን ፡ አንዳንድ የተዛቡ መረጃዎች፡ በምን ምክናያት ሊፈጠሩ፡ ቻሉ ምናልባትም፡ ከአቶ ሀብታሙ አለነ ጋር የተገናኜውን፡ ልታስረዳኝ ትችላለህ? ሲል ላቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ፡ በጣም ባጭሩ ልነግርህ እችላለሁ፡ የዚህ ሁሉ ውዝግብ ምክናያቱ፡ ይሄና ይሄ ብቻ ነው፡ በማለት የኖርወይን ነዋሪ ህዝብ፡ ጸረ ወያኔ እንቅስቃሴ፡ ከአንድ ግለሰብ ለዚያውም ሲዊድን በሚኖርና ኖርወይዎች መልኩንም እንኳን ከማያውቁት፡ ሰው ጋር በማያያዝ የብዙሀኑን ትግል ለማኮሰሥና ለማሣነሥ ሞክሯል። እኔ እስከማውቅው ድረስ እውነቱ ግን የኖርወይ ህዝብ ተቃውሞ ለግለሰብ፡ ብሎ ሣይሆን ኮንሰርቱን በወኪሉ በአቶ ደስታ ገ/ሥላሴ አማካኝነት፡ ያዘጋጀው ወያኔ ነው፡ የሚሰበሰበው ገንዘብ በቀጥታ የሚውለው፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ መግደያና ማፈኛ ነው፡ ከሚል እውነታ በመነሣት ነው።

4ኛ/ ወያኔዎች፡ እነሱን የተቃወመውን ሁሉ፡ ፖለቲካውን እንዳበላሸ፡ አድርገው በሚቆጣጠሩት ሚዲያ በማቅረብ፡ ሲያሰለቹን እንደኖሩት ሁሉ አርቲስቱም ማንም ሰው፡ ደግሞ የፓለቲካን፡ ጉዳይ የጠላውን ሰው የሚያወግዝበት፡ የወደደውን የሚያሞካሽበት፡ የግል መሣሪያ አይደለም፡ በማለት የቄሥ ሚስት አውቅሽ፣ አወቅሽ ቢሏት መጽሀፍ አጠበች፡ እንደሚባለው፡ ያለሙያው ገብቶ ፖለቲካ፡ ለማስተማር ዳድቶታል፡ ይሄም የሚያሣየው፡ የብዙሀኑን ጸረ ወያኔ የፓለቲካ ትግል ስሜትን፡ ለመግደል እያደረገው ያለውን ሙከራ ነው። ይህ ካልሆነ፡ ለመሆኑ ማነው ግለሰቡ? እሱ አብሮት የተሰለፈው አቶ ከስታ ገ/ስላሴ ወይንሥ ብዙሀኑ ሕዝብ? መልሱን ለአንባብያን እተወዋለሁ።

ነፃነትና ሙያዊ ሥነምግባርን በተመለከተ፡ አቶ ክንፉ አሰፋው፡ በተባው የብዕር ቱርፋቱ፡ የገለጸው ሥለሆነ አልገባበትም። ለማጠቃለል፡ ግን አርቲስት ቴዲ አፍሮ፡ ኖርወይን አስመልክቶ የሰጠውን ቃለ ምልልስ የተከታተላችሁ፡ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፡ ቲዎድሮስ ካሣሁን የተናረረው፡መስመሩን የሣተና ትክክለኛ፡ ያልሆነ፡መሆኑን ነው።

አዎ እየተካሄደ ያለው ትግል ነው፡ በአንድ ትግል ውስጥ ደግሞ፡ አብሮ የተሰለፈው ሁሉ አብሮ እንደማይዘልቅ፡ እሩቅ ሣንሄድ፡ ካለፈው 30 እና 40 አመታት የትግል ተሞክሮ፡ መረዳት እንችላለን። እንደ ዴንማርኮች፡ የአመርቂ ውጤት ባለቤት ለመሆንም፡ ከብዛት ይልቅ በጥራት ላይ ቢተኮር፡ መልካም ይመስለኛል።

ሞት ለወያኔና ለካህዲዎች!!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!!

matebemelese@yahoo.com